★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 37 **ቁጥር** 3 **የካቲት/መጋቢት** 2004 **ዓ.ም**

# ቀዳማዊ የካቲት በዳግማዊ የካቲት ይተካ

የካቲት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት ዓ.ም.፣ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ከፍቶ ሄዷል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከመጀመሪያዎች አንቀጾች የጎላ የታሪክ ኮቴ አስመዝግቦ ያለፈው፣ የሀገሪቱን ዜጎች፣ በዘር፣ በነገድ፣ በሃይማኖት እና በሌሎችም ሰው ሰራሽ መስፈርቶች ሳይከፋፍል፣ ሁላቸውንም በአንድ ላይ አስተባብሮ የኢትዮጵያን አብዮት እንዲፈጥሩ ማድረጉ ነበር። የካቲት አብዮት የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ሀብቱን ንብረቱ ፣ ተስፋውን ራዕዩ፣ ታሪኩን የአንድነቱ ማረጋገጫና የዜግነቱ መለያ በመሆኑ፤ በዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊ የታሪክ ቦታውን ይዞ ይናራል። ቢሆንም፣ ዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ዘለዓለም እንድትኖር ከተፈለገ ፣ ለትንሣኤ ኢትዮጵያ መታገል የግድ ይላል። በሞትና በሽረት መካከል የምትጠራሞተው የዛሬይቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘረኞች ፖሊሲ ጠፍታ እንዳትጠፋ ሁሉም ዜጋ ተባብሮ ሊያድናት ይገባል። ምክንያቱም፣ የየካቲት ስድሳ ስድስቱ አብዮት ዓላማና ራዕይ ፣ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊነቷን ጠብቃ በነፃነት በአንድነቷ ተከብራ እየበለፀገች እንድትኖር ስለነበረ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርቡ ዘመናዊ ታሪኩ አንድነቱን ያረጋገጠበት ታሪካዊ ወቅት ቢኖር፣ የየካቲት ስድሳ ስድስት አብዮት እንደነበር መላው የሀገሪቱ ሕዝብ የሚስማማበት ሐቅ ነው።

የየካቲት ስድሳ ስድስት አብዮት ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ ፣ ከገጠር እስከ ከተማ፣ በለውጥ አዋጅ ጠርቶ በማስተባበር፣ አንድነቱንና የጋራ ታሪኩን እንደገና ያረጋገጠበትን የወደፊትንም ብሔራዊ ተስፋውንና ራዕዩን በጋራ ለመተለም የተነሳሳበት ሀገራዊ ማኅተሙ ነበር። በመሆኑም፣ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ብሔራዊ ሀብት በግል የማንም ቡድን ፣ ክፍል ፣ ጎሳና ወገን ሊሆን አይችልም።

የየካቲቱን 66 አብዮት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ክብርና ቦታ የሚሰጠውም፣ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ የደም ዋጋ ስለከፈለበትም ጭምር ነው። ያ ጀግና ትውልድም ከጀግኖች ወላጆቹ በወረሰው የሀገር ፍቅር ስሜት ተነሳስቶ፣ ላስተማረውና ላሳደገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውለታ ለመክፈል በገባው ቃል ኪዳን መሠረት የመጨረሻ መሥዋዕትን እየገበረ አልፏል። ይህን የደም ዋጋ ሲከፍልም፣ ለአንድ ብሄር ወይም ክልል ብቻ ሳይሆን ለመላዋ ኢትዮጵያ፣ ለዜጎቿ ክብር፣ ነፃነት፣ ዕድገትና ብልፅግና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለፍትኅ-ርትዕ ሲል ነበር። ከጭቆና ሥርዓት ለመላቀቅ ፍቱን መድኃኒት ሆኖ የተገኘው መራራ ትግል ማካሄድ ብቻ ስለነበር፣ ትግሉ የጠየቀውን ሁሉ መሥዋዕት ሊከፈል የተቻለውም በዚህ መሠረታዊ ዕምነት ነበር። ያ ሀገር ወዳድ ትውልድ ለሚወዳት ሀገሩን ለሚያፈቅረው ሕዝብ ማንነቱን፣ አይከፍሉ መሥዋዕት በመክፈል አስመስክሯል። በመሆኑም፣ የካቲት ስድሳ ስድስት የኢትዮጵያ አብዮት የተገነባው በኢትዮጵያ ልጆች ደምና አፅም መሆኑን ተተኪው ትውልድ በሚገባ ይገነዘበዋል። በሀገሪቱ የታሪክ ምዕራፍም የአንፀባራቂ ኮከብ ቦታዉን እንደያዘ ይቀጥላል። ይህንን አንፀባራቂና ገናና በደም የተፃፈ ታሪክ ማንም አልፎ ሀጂና ረጋ-ሰራሽ ቡድን እንዲበክለው አይፈቀድለትም። ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ማህፀን የተፈጠረ በመሆኑ፣ ክንዱን ሳይንተራስ፣ ሀገሩ የዘረኞች መጫወቻ ሆና አትቀርም። እልህ አስጨራሹንና መራራ ትግሉንም ሳይበገር የቀጠለው በዚህ መሠረታዊ ዕምነቱን ቃል ኪዳኑ ነው። ይህንንም ዕውነታ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአድናቆትና በኩራት ይቀበለዋል።

በአለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት የጊዜ ክልል ያለፈው ትውልድ፣ በኢትዮጵያ የተፈራረቁትን ሦስት ሥርዓተ አገዛዞችን አይቷል፡፡ ሦስቱም ሥርዓቶች፣ ከአንድ የአገዛዝ ፅንፍ ወደሌላ ፅንፍ የተፈራረቁ ቢመስሉም፣ በሥረ መሠረታቸው ግን አንድ አካል አንድ አምሳል እንደሆኑ ከድርጊታቸውና ከምግባራቸው ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ቢሆንም፣ ሁለቱ ሥርዓቶች በባኀርያቸው ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ብዙ የሚያከራክር እንዳልሆነይገመታል፡፡ ሌላው ቢቀር ሀገር በመሸጥና የሕዝብን ታሪክ በማዋረድ ደረጃ የሚወቀሱ አይሆኑም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ወደ ሥልጣን ለመጡበትና ሥልጣን ላይ ለቆዩበት ሁኔታ የሚሰጡት ምክንያት የተለያዩ ቢሆኑም እንኳ፣ የዲሞክራሲ ባኀርይና ምግባር ስላልነበራቸው፣ ዜጎችን እየጨቆኑ በመግዛት አኳያ፣ በተመሳሳይ ረደፍ ይሰለፋሉ፡፡ ሥልጣንን ለመያዝና ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ዘዴና ብልሀት ለመጠቀም የየራሳቸው ማጠየቂያዎች ነበሯቸው፡፡ የመጀመሪያው፣ ስዩመ መለኮት ነኝ ብሎ በመስበክ፣ ዕምነትንና ባኀልን ሽርቦ በመጠቀም የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን አስፍኖ እስከ የካቲት 1966 ዓ. ም ሕዝባዊ አብዮት ድረስ ህይወተን አራዝሞ ቆይቷል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሕዝብን ትግል በመስረቅ፤ ለሕዝብ ቆሚያለሁ እያለ በውጭ ህሃይሎች ትብብር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልደገፈው ፣ ያልመከረበት፣ ከእምነቱ፣ ከባህሉ፣ ከታሪኩና ከመስተጋብሩ ጋር ያልተዋሀደ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አስፍኖ ለፋሽስታዊ ሥርዓቱ መስፍን ተጠቀሞ፣ ምናልባትም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳደሪ የሌለው የንፁሃን ዜጎች ደም እንዲፈስስ አደረገ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ለሀገር ለወገን የሚጠቅሙትን ታዳጊ ወጣቶች፣ ሊቃውንት ምሁራን፣ ሀገር ወዳድ አርበኞች፣ አዛውንትትን የሃይማኖት መሪዎች ፣ የሀገሪቱን ዳር ድንበር የሚያስከብሩትን የመከላካያ ሠራዊት ፣ የመስመርና ከፍተኛ የጦር መኮንኖች እና ጀግና ጀኔራሎችን ጭምር፣ ህፃናትና አረጋውያን ሁሉ ሳይቀር እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸውን መተራቸው፡፡ ሀገሪቱንም መና አስቀራት፡፡ በዘር ተደራጅቶ ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በነገድ ለመከፋፈል ለተደራጀ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ሀገሪቱን አጋልጦ ሄደ፡፡ ለዚህም ነው ታዲያ ዛሬ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡

“ክፍት ይዋል ክፍት ይደር ብለው ሲመርቁ
ቤቱም ክፍቱን ቀረ ሰዎችም አለቁ፡፡”

እያለ የብሶት እንጉርጉሮውን የሚያሰማው፡፡ ግን፣ ብሶቱንና ብስጭቱን፣ ጥቃቱንና ውርደቱን፣ ለመወጣት ዳግማዊ የካቲት እንደሚፈጠር ማንም ዜጋ ሊጠራጠር አይችልም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ወጥ የሆነውን የራሱን ዳግማዊ የካቲት በመፍጠር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ያመጣል እንጅ፣ አብዮትን እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ አያስገባም፡፡

የእያንዳንዱ ሀገር ሕዝብ የየራሱ የሆነ የግል በኀርይ፣ ታሪክ፣ ራዕይ፣ ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቂያ ስልት ፣ የኑሮ ዋስትናም ሆነ ሥርዓተ መንግሥት የመመስረት ዘዴ፣ ብቃትና ችሎታ ስለሚኖረው፤ ከባዕድ ጣቃ ተቀድዶ የሚሰፋለትን ጥብቆ ሊለብስ አይችልም፡፡ የወያኔንም የዘር የጎሳ ጥብቆ ሊያጠልቀው ቀርቶ ለማየትም የማይፈልገው ከዚህ ሐቅ በመነሳት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በውስጥ ከሃድያን የሚሰፋለትንም እጀ ጠባብ ለመንካት ቀርቶ፣ ለማየትም እንኳን ጭራሽ አይፈልግም፡፡ ይህንንም ዕውነታ በደርጉ አስራ ሰባት ዓመት ጭቆናም ሆነ በጠባብ ብሄረተኞች የሃያ ዓመታት አገዛዝ አስመስክሯል፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቱ ትውልድም ፣ የወያኔ ከፋፋይ ሴራ እያከሸፈ ፣ የሚዘምረው የአመፅ ትግል ፣ በሚከተለው የአንድነት ሰንደቅ ሥር ነው፡፡

እስላም ክርስቲያኑ የቆላው የደጋ
ለወያኔ ተንኮል እንዳትሰጠው ዋጋ፤
ትግላችንን ይዘናል ክረምት ከበጋ
ሀገር፣ ሕዝብ ለማዳን ከጥፋት አደጋ

የሀገራችን ሕዝብ ፣ ከሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት የዓለም ዓቀፍ ክስተትና ነባራዊ ሁኔታዎች ውጭ እንዲያስብና እንዲቀበል አይጠበቅበትም፡፡ አንድ ሰው አንድ ድምፅ በሚለው የዴሞክራሲ መርኅ እንዲመራ የሀገራችን ሕዝብ ዕድልና መብት ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ መሠረታዊ የዴሞክራሲ መብት ደግሞ ከማንም ኃይል የሚሰጠው የዕርጥባንን የምፅዋዕት ችሮታ ሳይሆን፣ በራሱ ታግሎ የሚያገኘው ይሆናል፡፡ የደም ዋጋ እየከፈሉ ነፃነትና ማስከበር ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ዳግማዊ የካቲትን ተከትሎ በሚመጣው የኢትዮጵያ ፀደይ በድል ይጠናቀቃል፡፡ የሰሜን አፍሪካን የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች አምባገነኖችን ለማስወገድ የራሳቸውን (የአረብ ፀደይ) እንደተጠቀሙ ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደዚሁ ፣ ወራቱን ጠብቆ በሚመጣውና በሀገሩ የፖለቲካ መልክዓ ምድር በሚፈጠረው ሕዝባዊ አመፅ ኢትዮጵያዊ

ማንነቱን እያስመሰከረ አምባገነኖችን ያስወግዳል። ባዕዳንም፣ ይህንን ሐቅ እንዲገነዘቡለት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳስባል! ይማፀናልም። ይህ የተማፅንዖ ድምፅ የሰማንያ ስምንት ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ነው። እኛም፣ ምንም እንኳን፣ "ዘላቂ ወዳጅና ጠላት የሚባል ነገር የለም፣ ሊኖር የሚችለው ዘላቂ ጥቅም ብቻ ነው።" የሚለውን የዲፕሎማሲ ይትበኃል በሚገባ ብንገነዘብም፣ አንድን ብሔር እውክለላለሁ ከሚል ንኡሥ የብሔር ቡድን ይልቅ ፣ በሁለንተናዊ መስፈርት ሲገመገም ፣ ከሰማንያ ስምንት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መወዳጀት ዘለቄታ ይኖረዋል ብለን እንናገራለን። ከዚህ በተረፈ ግን፣ መለስን በሰዬ፣ ስብሀትን በአደዬ ለመለወጥ የሚደረግ ሽርጉድ፤ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግር አይፈታውም። የወያኔ ደጋፊዎች ባዕዳን፣ ይህንን ሐቅ ሊገነዘቡት ይገባል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በሀገሩ የውጭም ይሁን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገባበትን ሁሉ አጥብቆ የሚቃወመውም ከዚህ አብይ ምክንያት የመነጨ ነው።

ከፍ ብሎ ከሰፈረው አንቀፅ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁለት ሥርዓቶች ተከትሎ የመጣው ይህ ዛሬ ኢትዮጵያን እያወደመና እየበዘበዘ ሀብት እያሸሸና እራሱንም እያበለፀገ፣ ዜጎቿንም እያደኸ፣ በዘር እየከፋፈለና እያዋረደ የሚገኘው በትግራይ ሕዝብ ስም የተደረጀው የወያኔ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን ነው። ይህ ጠባብ የአድጎሮት ቅሪት ፣ በአምባገነንነቱ ከሌሎቹ ሁለት ሥርዓቶች ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፣ እናም ደግሞ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ባይካድም፣ ከእነርሱ የሚለይበት በርካታ የማንነት መግለጫዎች አሉት። ከሁሉም በላይ የመሠረታዊ ማንነት መታወቂያው፣ የኢትዮጵያ ዋልታና ማገር የሆነውን የትግራይን ሕዝብ ከመላዋ ኢትዮጵያ ለመገንጠል መመሥረቱን መታገሉ ብቻ ሳይሆን ፣ ሌላውን የኢትዮጵያ አካል የሆነውን ሕዝብ ማስገንጠል መቻሉም ጭምር ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድርግ ደግሞ ፣ ወያኔ ፣ ከኢትዮጵያ ታሪካዊና ቀንደኛ ጠላቶች ጋር ተባብሮ ብሄራዊ ክኅደት ፈፅሟል። በታሪክ ፊት አሳፋሪና አዋረጅ የሆነውን ይህን ታላቅ ክኅደት በመፈፀሙ፣ የውጭ ጠላቶች በኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ የእጅ አዙር ወረራና ጥቃት እንዲያከናውኑ አመቻችቶላቸዋል። የኢትዮጵያን መንበረ መንግሥት ጨብጦ፣ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለውጭ ባዕዳን አሳልፎ የሚሰጥ ቡድን በመሆኑም፣ ወያኔን ከሌሎቹ ሁለት ሥርዓቶች በእጅጉ ይለያል። ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር፣ በመከራወም ሆነ በደስታው ዘለዓለም አብሮ የኖረን ሕዝብ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ግንኙነት የለኸምና ወደ አሻህብት ሂድ ብሎ በክኅደት ፊርማ ማባረር ፣ እርሱ ከተካቸው ሁለት ቀደመት አምባገነኖች በተለየ ከታሪክ ጉድፍ ውስጥ ከትቶታል።

"በሥልጣን ላይ የሚቀመጡ ሁሉ ታሪክን እንዳሻቸው ይለቀልቁታል።" ቢባልም፣ ወያኔ ግን የሀገራችንን ታሪክ ለመሥራትም ሆነ ለመፃፍ የሞራል ብቃትም ይሁን ኢትዮጵያዊ ስብዕና አይኖረውም። ለምን ቢባል ፣ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን ያዋረደ ከመሆኑም በላይ፣ ተዘርዝሮ የማያልቅ ብሔራዊ ወንጀል እየፈፀመ ያለ ቡድን በመሆኑ ፣ የዜግነቱን ክብርና ማዕረግ እርሱ ራሱ በገዛ እጁ ስለገፈፈው ነው። የሀገር ተወላጅ ዜጋ ሆኖ ፣ እንደ ባዕድ ሀገር ሰው ለራስ ሀገርና ሕዝብ ቀንደኛ ጠላት ሆኖ በመገኘት የራስን ሀገር መሸጥ ፣ በሀገራችን የመንግሥት ታሪክ ሂደት ወያኔ መጀመሪያው መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝግቦ ይዞታል። ዛሬ፣ እኛ የካቲት ስድሳ ስድስትን የኢትዮጵያን አብዮት ስንዘክር ፣ ከአብዮቱ ወዲህ የተፈራረቁትን የሦስት አምባገነን ሥርዓቶች ማንሳት የግድ ስለሆነብን ነው እንጅ፣ ስለወያኔ ተግባርና ማንነት መግለፅ አንገብጋቢ ሆኖ ስለተገኘ አይደለም። ከዚህም በላይ፣ የግድ ታሪካዊውን የካቲት ስድሳ ስድስት ዘክሮ ለወጣቱ ትውልድ ለመመዝገብ በይበልጥ፣ ኢትዮጵያዊነታችን ያስገድደናል። ማንነቱን፣ በግብሩና በባኅርዩ የገለፀ አገር አጥፊ ቡድን መሆኑን ሕዝባችን ጠንቅቆ ያውቃልና፤ ይህንንም ዘወትር ማንሳት፣ ውሃ ከመውቀጥ ያለፈ እርባና የለውም።

በየጊዜው የሚነሱ የአምባገነን ሥርዓቶች ለሥልጣን መቆናጠጫና መቆያ የሚሆናቸውን ዘዴ በመሸረብ፣ ሕዝብን መደለያና ማወናበጃ ፕሮፓጋንዳ እንደሚጠቀሙ ሁሉ፣ የባዕዳንን ጥቅም ለማስፈፀም የተቋቋመው ወያኔም ፣ የራሱን ማወናበጃ ዘዴ ይጠቀማል። ለዚህም ሁለት ጣምራ ማታላያዎችን ይዞ ቀርቧል። እነርሱም፤ **አብዮታዊ ዴሞክራሲና የጎሳ ፌዴራሊዝም** የሚባሉ አስቂኝ የቁማር መጫዎቻ ካርታዎች ናቸው። ሁለቱም መጫወቻዎች ፣ ዴሞክራሲም ሆነ ፌዴራሊዝም ባሉዋሉበት ያልዋሉ ፣ በባኅርይም ሆነ በተግባር የዴሞክራሲንም ሆነ የፌዴራልን መንፈስና ዓላማ የማያንፀባርቁ የባዶ ጩኸት አስተጋብያዎች ናቸው። ለዴሞክራሲ መብት፣ ለሰዉ ልጆች ነፃነት፣ ለፍትኅ ርትዕ ያልቆሙ፤ ለጋራ ልማትም ሆነ ለሕዝብ ብልፅግናም ይሁን ለሀገር ዕድገት የማይጠቅሙ እንደቀትር እሳት ሕዝብን የፈጁ ሀገርንም የሚያጠፉ ናቸው። የባዶ ነህስ ጩኸት ከመሆን አያልፉም። መልከ ጥፉን በስም ለመካስ የሚደረግ ከንቱ ወዳሴ ካልሆነ በስተቀር ፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተባለው ከዴሞክራሲ ሥርዓትና ፍልፍስፍና ጋር የተጣላ

ከመሆኑም ባሻገር፣ ለዜጎች ነፃነት፣ ለሰብዓዊ መብት መከበር ፣ ለህግ የበላይነትና ለአንድ ሀገር ዜጎች እኩልነት ያልቆመ ድይን ፍልስፍና ነው። የዴሞክራሲ ሥርዓት ዓይነተኛ መግለጫ የሆነውን መድበለ ፓርቲን ስለሚፃረር፣ የሌሎች ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ አምርሮ ይፈራል። ይህም ጠባዩ ፣ ለአምባገነን ሥርዓት አራማጆች የተቀበዝባዥነት ባኅርይ መገለጫ ሆኗል። ለሕገ መንግሥታዊ ዴሞክራሲ የማይገዛም በመሆኑ፣ ለአምባገነን ሥርዓት አራማጆች የመጨቆኛ መሳሪያ ከመሆን ስለማያልፍ፣ ዜጎች ሁሉ አምርረው ይቃወሙታል። በዚህ መሠረታዊ ዕውነታ ምክንያት፣ አብዮታዊ መሆኑ ቀርቶ፣ የአድኀሮት ኃይለት ዝባዝንኪ አውደ ንባብ ከመሆን አይዘልልም።

የወያኔ የጎሳ ፌዴሬሽንም እንደዚሁ፣ ከራሱ ዘረኝነት ባኅርይን ዓላማ ጋር የተዋኀደ ስለሆነ ሲታገልበት የነበረውን ዓላማ ለማስፈፀም የተዘጋጀ እንጅ ፣ የብዙ ብሔር በሔረሰብ ለሆነችው ኢትዮጵያ ለዕድገትም ይሁን ለብልፅግና የሚጠቅም እንዳልሆነ ባለሙያዎች ሁሉ ይስማሙበታል። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ለሚኖር ሕዝብን ሀገር፣ የወያኔ የክልል ፌዴሬሽን ለአስተዳደርና ለፍርድ አሰጣጥ ቅልጥፍናም ይሁን የልማት እንቅስቃሴ የሚበጅ አይደለም። ዕርግጥ፣ የወያኔ መሪዎች፣ ሀገሪቱን ወደ ቅድመ ቴዎድሮስ ጊዜ እንደነበረችው ዘመነ መሳፍንት የጎጥን የክልል መንግሥታት ከፋፍለው ወደ ኋላ ስለመለሷት ፣ ኢትዮጵያ ወደ ሃያኛው ክፍል ዘመን መግባቷ አይታያቸውም። የጠባብነት መሠረቱ፣ በክልልን በብሔር ተኮድኩዶ በአጭር ተወስኖ መሪር ስለሆነ፣ ከአድማስ ባሻገር ለማየት የሚያስችለው ዓይነ ኀሊና አይኖረውም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የቆዳ ስፋት በተንጣለለው የሀገሩ መልከ ምድር በየትኛው ክፍለ ሀገር ያለምንም ገደብ ተንቀሳቅሶ ሰርቶና ነግዶ፣ አርሶና ከብት አርብቶ፣ አሳን አጥምዶ፣ ማዕድን ቆፍሮ፣ ተምሮ አስተምሮ ፣ አየሩን ቀስፎ ፣ ባኅሩን ጠልቆ፣ ተራራውን ወጥቶ ከአድማስ ባሻገር የማየትና የመመራመር መብቱ ፣ በጎሳ ፌዴሬሽን ሊወሰን አይችልም። አይገባውምም። የኢትዮጵያ፣ ሕዝብ የወያኔና የጎሳ ፌዴራሽን አንቅሮ የተፋው ይህንን የዜግነት ፀጋውን ብቻ ሳይሆን፣ ሰብዓዊና የተፈጥሮ መብቱንም ስለገፈፈው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአያሌ ዘመናት በአንድ ላይ ተባብሮና ተዛምዶ በኅብረት ሊኖር ከአስቻሉት ዓይነተኛ ምክነያቶች አንዱ፣ በመላው ሀገሩ ከአጽናፍ እስከ አፅናፍ ያለስጋት እየተዘዋወረ ከማንኛውም ዜጋ ጋር እንደልቡ በመገናኘት ነበር። ይህ ግደብ የለሽ ነፃነት ግን ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በወያኔ የጎሳ ፌዴራሽን ሊገደብ ባልተገባው ነበር። የሰውን ልጅ በጎጥና በዘር ከልሎ፣ ከሌላ ዜጋው ጋር በንግድ፣ በጋብቻና በማኅበራዊ ኑሮ፣ በባኅሉና በሃይማኖቱ እየተሰባሰበ፣ በሌሎቹም የሰውን ልጅ በሚያዛምዱ ሕዝባዊ ሁል-አቀፍ ግንኙነቶች ያለገደብ መገናኘት ለዜጎች አንድነትና ለሀገር ዕድገት መሠረታዊ ነው። በኢኮኖሚ ጠበብቶች ትንታኔም ቢሆን ፣ ድኅነትን ለመዋጋትም ሆነ የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ የጎሳ ፌዴሬሽን ዕንቅፋት መሆኑን በአሳማኝ መረጃ በተደገፈ ምርምር የተረጋገጠ ሆኗል። ለዚህም ነው፣ የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ ብሔርን መሠረት አድርጎ የተዋቀረ ፌዴሬሽን፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓትም ይሁን ለሀገር አንድነት፣ ለዜጎች ብልፅግናም ሆነ ድኅነትን ለማሰወገድ እንቅፋት የሆነው።

መንግሥት የሚባለው ተቋም ምንም ዓይነት ተፈጥሮ፣ ይዘትና ቅርፅ፣ እንዲሁም ባኅርይና ድርጊት ይኑረው፣ በአንድ ሀገር ውስጥ ከፍተኛውን የድርጅት ቅርፅን መዋቀር የያዘ ተቋም መሆኑ ግን ለክርክር የሚቀርብ አይሆንም። ታዲያ፣ይህን ከፍተኛ ድርጅታዊ ቅርፅ የያዘ ተቋምን፣ በአንድ ሀገር ውስጥ ሊገኝ/ሊኖር የሚችለውን ሁለንተናዊ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ፤ ለኛ የማትሆን ሀገር ትበጣጠስ ብሎ ሀገርን መቆራረስና ሕዝብንም በጎሳ መከፋፈል ፣ ከዜግነት የሚመነጭ ባኅርይ ሳይሆን፣ እንደ ዕንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ፣ እንደ ባዕድ ወራሪ መራሽ ፣ እንደ ቀትር እባብ ነካሽ እንደ ማታ ጥላ ከስሞ የሚቀር ይሆናል። ያጠባውን ጡት የሚቆርጥና ያጎረሰውን ጣት የሚነክስ ፀላዒ-ሰናይት ሁሉ እርጉም በመሆን ከምድረ ኢትዮጵያ እንደሚጠፋ የታሪክ ሐቅ ነው። ይህም ሐቅ በዳግማዊ የካቲት ሕዝባዊ አመፅ እንደገና መረጋገጡ አይቀሬ ነው።

እኛ፣ የየካቲት ስድሳ ስድት አብዮትን መነሻ ፣ ሂደቱንና መድርሻውን ማየት የምንችለው የትግላችን አልፋ አድርገን ከተነሳንበት ከኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅምና ከሀገራችን ኢትዮጵያ ነፃነትና ብሔራዊ ልዕልና አኳያ ነው። ይህ በጊዜና በቦታ የማይለዋወጠው የትግላችን ስንደቅ ምን ጊዜም ህያው እንደሆነ ፣ የዓላማችን መርኀ ሆኖ ይኖራል የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ መብቱን በማያሻማ መንገድ እስካረጋገጠ ድረስ ማለታችን ነው። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም የፖለቲካ ውሽንፍር ሰለባ ሳንሆን፣ በወቅቱ የኃይሎች አሰላለፍና የዲፕሎማቲክ ብወዛ ሳንደፈርና በሀገራችንም ብሔራዊ ጥቅም ሳንደራደር ከመታገል የተለየ አጀንዳ ሊኖርን

እንዳማይችልም ከሕዝባችን የበለጠ ሕያዊ ምስክር የለንም።

የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል በትኖ፣ ደርግ ሀገሩንና ሕዝቡን ለአገር አፍራሾች ጥሎ ሲሸሽ፤ ወያኔ አዲስ አበባ የገባው በእኛ ሬሳ ላይ ተራምዶ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል። ወያኔ ይህን ሊያደርግ የበቃወም ፣ በውጭ ባዕዳን ኃይል በመደገፍና በከባድ የጦር መሣሪያና ታንክ ታጅቦ ነበር። ኢሕአፓ፣ በባዕድ ጦር እየታጀበ የሀገሩን ጥቅም ለባእድ አሳልፎ መስጠት ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ ስለአልፈቀደለት ይህንን ከማድረግ ተቆጥቧል። ወደፊትም ይህንን አይሞክረወም ኢሕአፓ፣ አምባገነንንና የሀገር መከላከያ ሠራዊትን በአንድ አይፈረጅምና! ይህንን በመርህ ላይ የተመሠረተን ጠንካራ አቋም ፣ የሚያወቅ ያውቅለታል። ሌላውም እንዲረዳው ይጠይቃል። ይህ የአገርንንና የሕዝብን ፍቅር መሠረት ያደረገ አቅዋም በሕይወት የተረፉት ብቻ ሳይሆን፣ የገቡትን ቃል በመጠበቅ የሰማዕትን ክብር የተጎናፀፉት የዚያ ጀግና ትውልድ አባላት ጭምር ቅርስ ነው። ከዚህ መርሃ ግብር በመነሳት፣ እኛ የመሥዋዕትነት ዕድል ሳናገኝ በህይወት ቆይተን የምንታገለው ፤ የኢሕአፓ አባላትም ፣ የሀገራችንን ሕዝብ፤ ጠይቅ-ተጠየቅ እንላለን! ይህንን የምንለውም ግዴታችንን እየተወጣን መብታችንን ለማስከበር ነው።

የየካቲት ስድሳ ስድስትን የኢትዮጵያ አብዮት የምንዘክረው ፦

1. የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ከመቸውም በበለጠ እጅግ ውስብስብ በሆኑበት ወቅት፣ የትግሉም ጉዞ ከምን ጊዜውም በላይ መራራና ጠመዝማዛ እየሆነ በሄደበት ዘመን፤
2. የኢትዮጵያ የወስጥና የውጭ ጠላቶች ሕዝባችንን ከፋፍለው የሀገር ሀብት ለመበዝበዝ መልካም አጋጣሚ ባገኙበት ወቅት፤
3. ከፋፋይ ኃይሎች ዓላማቸውን ለመምታት አመች ጊዜና ሁኔታ በተመቻቸላቸው ሰዓት፣
4. ለኢትዮጵያ ነፃነትና ኅልውና የቆሙት የአንድነት ኃሎች ሊተባበሩ ባልቻሉበት ዘመን፤
5. በየካቲት አብዮት የተነሱት የሕዝብ ጥያቄዎች በቂ መልስ ባላገኙበት ሁኔታ፤
6. የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡**የመሪ ያለህ** !፡ በማለት ሀገሩን ከወያኔ የዘረኛ አገዛዝ ሊያወጣለት የሚችል ኢትዮጵያዊ ኃይል ለማግኘት በሚጓጓበት፤

ሰዓት ነው።

በመሆኑም፣ ትግላችንን ለመቀጠል የበለጠ መሥዋዕት የሚጠይቅ መሆኑን በሚገባ ስለምንረዳ፤ ለሀገራችን ነፃነትና ሉዓላዊነት፣ ለሕዝባችን እኩልነትና አንድነት፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት የቆሙ ሁሉ ያላቸውን ልዩነት እያቻቻሉ እንዲተባበሩ ጥሪ እናስተላልፋለን።

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!

ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!